ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መልዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር ስምንት ጳጉሜ 2012 ዓ/ም

# ተስፋ!

በሰብአዊ መብት ጥሰት ከተጠያቂነት ያለማምለጥ መርሆዎች...

በህግ አምላክ

የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን...



# ርእሰ አንቀጽ

ኢሰመጉ

# በሕግ አምላክ!

ባለፈው ሰኔ ወር መጨረሻ እውቁ የኦሮምኛ ሙዚቀኛ ሀጫሉ ሑንዴሳ ሕይወቱ በግፈኞች ማለፉ ይታወሳል፡፡ ድርጊቱን ተከትሎም በአዲስ አበባ እና በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች የተከሰተው ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ጥፋት እጅግ አሳዛኝ ነው፡፡ ዜጎች ለዘመናት በኖሩበት ቀዬ ከለላ በማጣታቸው ለድርብርብ ጥቃቶች ተጋላጭ ሆነዋል፡፡ በሀገሪቱ ማኅበረ-ፖለቲካ ውስጥ አዲስ ክስተት በተፈጠረ ቁጥር በየአካባቢው የሚገኙ ኅዳጣን ቡድኖች ዓይነተ-ብዙ ለሆኑ ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ቀውስ ሰለባ የመሆናቸው ሂደት በዚህ ‹‹የለውጥ አመራር›› ጊዜ እጅጉን ተደጋጋሚ እና የተለመደ ሆኗል፡፡


መንግሥት በእንዲህ ያሉ ወቅቶች ሕግ እና ሥርዓትን ለማስከበር የሚያሳየው መለሳለስ፣ ባስ ሲልም ራሱን እንደ ተበዳይ እና ተጎጂ አድርጎ የማቅረብ ልማዱ ነገሮች የበለጠ ውስብስብ እና አስቸጋሪ እያደረገው ይገኛል፡፡ ሰሞኑን ደግሞ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች በተደረገ ተቃውሞ የመንግሥት ጸጥታ ኃይሎች እርምጃ ወስደዋል፡፡ የእነዚህ እርምጃዎች ሕጋዊነት እና ተመጣጣኝነትም በብዙዎች ዘንድ ጥያቄ ቢያስነሳም፤ የክልሉ መንግሥት ሕጋዊ እና ተመጣጣኝ እርምጃዎች ናቸው የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ይህም የወቅቱን የሀገራችንን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ እያደረገው መሆኑን እና ወዳለፉት ጊዜያት እንዳይመልሰን ጥንቃቄ እንዲደረግ ኢሰመጉ በጽኑ ይጠይቃል፡፡

ያለፉት ሁለት ወራት በእነዚህ ክስተቶች ብቻ አልነበረም ያለፉት፤ ይልቁንስ በደቡብ ክልል ወላይታ ዞንም የከፉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ እጅግ ድምጻቸው ከሚሰሙ ጉዳዮች አንዱ እና ዋነኛው በተለይም በደቡብ ክልል የሚገኙ በርካታ ማኅበረሰቦች በክልል የመደራጀት ሕገ-መንግሥታዊ ጥያቄ ማንሳታቸው ነው፡፡ ከእነዚህ መካካል የሲዳማ ብሔር በክልል የመደራጀት የዓመታት ጥያቄ ከብዙ ቀውሶች በኋላ በሕዘበ-ውሳኔ ምላሽ አግኝቶ፣ ክልሉ በይፋ ራሱን አደራጅቷል፡፡

ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ከቀደሙት ስህተቶች በመማር ዘላቂ መፍትሔ ያገኛል ተብሎ ሲጠበቅ በቅርቡ ደግሞ በወላይታ ዞን ተመሳሳይ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በዜጎች ላይ ተፈጽመዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ አመራሮች እና ሌሎችም ግለሰቦች በዞኑ ዋና ከተማ ሶዶ ጉተራ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በስብሰባ ላይ ሳሉ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ መደረጉን ተከትሎ፤ በሶዶ፣ በቦዲቲ፣ በአረካ እና በሌሎችም የዞኑ አካባቢዎች ተቃውሟቸውን ለማሰማት አደባባይ በወጡ ዜጎች ላይ የኃይል እርመጃ በመወሰዱ የበርካታ ሰዎች ሕይወት ተቀጥፏል፣ አካልም ጎድሏል፡፡

ለሰብዓዊ መብቶች ቀውስ ሰበብ ፈላጊው ፖለቲካችን የሚታከምበትን ዘላቂ መፍትሔ በጎን ማፈላለጉን ለአፍታም ቢሆን ሳይዘነጋ፤ ሁሉም ዜጋ ሕግና ሥርዓት የሰፈነባት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ዋስትና የሚሰጡ ተቋማት የተገነቡባት፣ የፖለቲካ መጫወቻ ሕጉ ዲሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት ብቻ የሆነባትን በጠንካራ ማኅበረ-ፖለቲካ ላይ የተመሰረተች ሀገር የማቅናት ሂደቱን እንዲያግዝ፣ የድርሻውን በጎ አስተዋጽዖ እንዲወጣ እና በጽናት እንዲታገል ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡ መንግሥትም ሕግን አክብሮ፣ ሕግ እንዲያስከበር ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

…//…



## መልእክተ ኢሰመጉ

አሳታሚ
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች

ዳን ይርጋ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም

### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢ.ሜል= info@ehrco.org

ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፤ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

## ሰብዓዊ መብት

# በሰብአዊ መብት ጥሰት ከተጠያቂነት ያለማምለጥ መርሆዎች እና የመንግስት ኃላፊነት በኢትዮጵያ

በያሬድ ኃይለማርያም

### መግቢያ፤

የሁለተኛውን የአለም ጦርነት ማክተም ተከትሎ በተቋቋሙት የኑረንበርግ እና የቶኪዮ የወንጀል ችሎቶች እና እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በአለም አቀፍ ደረጃ የታየው የጸረ-ከወንጀል ተጠያቂነት የማምለጥ ንቅናቄ (Anti-impunity movment) የአለም አቀፍ ሕጎችን እና አተገባበራቸውን ቅርጽ በማስያዘር እረገድም ሆነ በሚፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተጠያቂነት እንዲጎላ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። እስከ 1980ዎቹ መገባደጃ ድረስ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ የነበረው ልማዳዊ አሰራር አጥፊዎችን በስም ጠርቶ አድራጎታቸውን በአደባባይ የማንቋሸሽ (publicly naming and shaming) ነበር። ይህም ሂደት በልማዳዊ አሰራር ከፍተኛ የመብት ጥሰት የፈጸሙ አካላት ጭምር ከህግ ተጠያቂነት የሚያመልጡበትን ወይም ነጻ የሚሆኑበትን የዘልማድ የምህረት አሠራር ፈጥሮ ነበር። በ1990ዎቹ የእጀመረው ንቅናቄ ግን ይህ ልማድ እንዲቀየር እና ግለሰቦችም ከባድ በሆኑ የመብት ጥሰት አድራጎቶች በአለም አቀፍ የወንጀል ሕግ እንዲዳኙ አድርጓል። በዚህም ምክንያጥ ያለንበትን የ21ኛው ክፍለ ዘመን፤ የተጠያቂነት ዘመን ወይም "age of accountability" ተብሎ እንዲገለስ ምክንያት ሆኗል። ይሁንና በበርካታ የአለማችን ክፍል ሰብአዊ መብት የሚጥሱ አካላት ተጠያቂ አለመደረጋቸው እና ጥፋት ፈጽሞ ተጠያቂ ያለመደረግ ባሕል አሁንም በስፋት መቀጠሉ በሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ላይ ትልቅ እክል ከመፍጠርም አልፎ ከፍተኛ የሰብአዊ ቀውሶች ተባብሰው እንዲቀጥሉ ምክንያት ሆኗል።

ይህ ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶችን በመጣስ ተግባር ተሰማርተው እና ከፍተኛ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ የወንጀል አድራጎቶችን ፈጽመው ከተጠያቂነት ነጻ የሚሆኑበትን ወይም የሚያመልጡበትን አሥራር ወይም ሂደት በአገሮች የሰበአዊ መብት አጠባበቅ ላይ እያሳደረ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማስቀረት በማሰብም የተባበሩት መንግስታት እ.ኤ.አ በ2005 አንድ "UN Principles for the Protection of Human Rights Through Action to Combat Impunity" ተብሎ የሚታወቅ ሰነድም አጽድቆ አውጥቷል። ይህ የተባበሩት መንግስታት መርህ እየተባለ በአጭሩ የሚጠራው ሰነድ ከፍተኛ አለም አቀፍ ድጋፍ እና ተቀባይነትን በአጭር ጊዜ ውስጥም አግኝቷል። በአሁን ሰዓትም የከፋ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና ከፍተኛ ግምት በሚሰጣቸው አለም አቀፍ የበጎ አድራጎት ተግባራትን የሚደነግጉ ሕጎች ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን ለመከላከል ሰነዱ በሥራ ላይ እንዲውልም ተደርጓል። በአለም አቀፍ ደረጃም ወጥ እና ተመሳሳይነት ያለው የተጠያቂነት ልማድን ለማስረጽ ሲባል አገሮች በተለያየ መልኩ የግዴታ ስምምነት ውስጥ እንዲገቡ እና ጥፋት አጥፍቶ ያለመጠየቅ ከለላን ወይም ከተጠያቂነት የማምለጥ አሠራሮችን እንዲያስወግዱ በርካታ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። ይህ በተባበሩት መንግስታት ጸድቆ የወጣውና ከተጠያቂነት የማምለጥ ልማድን ለማስወገድ የወጣው የስምምነት ሰነድ በውስጡ በርካታ መርሆዎችን አካቷል። በርካታ ምሁራን ይህን መርህ ተኮር ሰነድ የክፍለ ዘመኑ ከፍተኛ የሞራል ሥነምግባር የተንጸባረቀበት ልዩ ስምምነት 'one of the unique ethical signqtures of our time' በሚል ይገልጹታል።

የከፋ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የፈጸሙ ግለሰቦች እና የመንግስት አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሂደት እና አሰራር በአለም አቀፍ ደረጃ ተጠናክሮ እንዲወጣ የተደረገበት ጥረት እና ሂደት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ እ.ኤ.አ. ከ1989 አንስቶ እስከ 2005 ዓ/ም ድረስ ያለውን ረዥም ጊዜ በመውሰዱ 'long decade' በመባልም ይታወቃል። ይህ ጊዜ በአለማችን ውስጥ በርካታ እና አስከፊ የሚባሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተፈጸሙበትም ወቅት ነው። የሩዋንዳው እና የዩጎዝላቪያ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች የተፈጸመው በዚህ ጊዜ ውስጥ ነው። በተለያዩ የአለማችን ክፍሎችም የጅምላ ጭፍጨፋዎች የተካሄዱበት ወቅት ነው። እነዚህን ተከትሎ በርካታ አለም አቀፍ እርምጃዎች ተወስደዋል፣ አዳዲስ አለም አቀፍ ሕጎች ወጥተዋል፣ አዳዲስ አለም አቀፍ ተቋማት እንዲመሰረቱም እነዚህ ክስተቶች ምክንያት ሆነዋል። የሰብአዊ መብት ጥሰት ፈጻሚዎችንም በወንጀል አድራጎት ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትም የተከናወኑበት ወቅት ነው።

ግለሰቦችን፤ በተለይም በከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የነበሩ እና አገር የመሩ እንደ የቀድሞው የቺሊ መሪ አጉስቶ ፒኖቼ እና የቀድሞው የሰርቢያ መሪ እስሎቦዳን ሚሎሶቪች ጭምር ሥልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን ለፈጸሙት ከፍተኛ የመብት ጥሰት በአለም

አቀፍ መድረኮች ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል። በበርካታ አገሮችም ይህ ተጠያቂነትን የማጉላት እንቅስቃሴ በስፋት የተተገበረ ሲሆን ብዙ አገሮች የእውነት እና ፍትህ አፈላላጊ ኮሚሽን በማቋቋም አጥፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ እና ተበዳዮችም የሚካሱበት አሰራር ዘርግተው የቆዩ የማህበረሰብ ቁስሎችን ለማከም ችለዋል። እ.ኤ.አ በ2005 በተባበሩት መንግስታት ጸድቆ የወጣው ተጠያቂነትን የማረጋገጥ መርህ ሰነድ ለዚህ አለም አቀፍ ንቅናቄ እና ለውጥ ጥሩ ማሳያም ነው። ከዚህ አለም አቀፋዊ እይታ በመነሳት በሰብአዊ መብት ጥሰት የተሳተፉ ሰዎችን ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሰራር እና ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በተከታይ ባሉት የዚህ ጽሁፍ ክፍል በመጠኑ እንመልከት።

## መሰረታዊ መርሆዎች እና ትርጉም፤

ከወንጀል ተጠያቂነት ማምለት ወይም በእንግሊዘኛ impunity የሚለው ቃል በውስጡ የያዘው ሃሳብ እና ትርጓሜው ባጭሩ የሚከተለው ነው፤ 'ሰብአዊ መብት ጥሰት በመፈጸም በወንጀል ሕግ፣ በፍትሐብሔር ሕግ፣ በአስተዳደር ሕግ ወይም በሥነ ምግባር ደንብ ሊጠየቅ የሚገባው ሰው ላይ ተገቢውን ምርመራ አለማካሄድ፣ ታስሮ መቆየት ሲኖርበት እንዳይታሰር ማድረግ፣ ክስ እንዳይቀርብበት እና ለፍርድ እንዳይቀርብ ማድረግ፣ በፍርድ ቤት ጥፋተኛነቱ እንዲረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ፣ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ የፍርድ ውሳኔ እንዳይሰጥበት እና ቅጣት እንዳይጣልበት ማድረግ፤ እንዲሁም ለተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል አለማድረግን ያካትታል።' በአጭሩ በእንግሊዘኛም እንዲህ በማለት ይተረጎማል፤ 'the imposssibility, de jure or de fqcto, of bringing the perpetrators of violations to account' ። የተባበሩት መንግስታት ያጸደቀ የመርህ ሰነድ በውስጡ 38 መርሆዎችን የያዘ ሲሆን መርሆዎቹንም በሦስት የመብት ማዕቀፎች ስር አድርጎ አስቀምጧቸዋል። የመጀመሪያው የማወቅ መብት (the Right to know)፣ ፍትህ የማግኘት መብት (the Right to Justice) እና ከተደጋጋሚ ጥቃት ነጻ ለመሆን በቂ ጥበቃ የማግኘት መብት (the Right to Repqrqtion/Guarantees of Non-Recurrence)።

Impunity ወይም ከወንጀል ተጠያቂነት የማምለጥ አሰራር ዋነኛ መነሻው መንግስት ከዚህ በታች ከተጠቀሱት አራት መሰረታዊ የሆኑ እና በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እና ግዴታዎቹ ውስጥ አንዱን ወይም ሁሉንም ለመከወን ያልቻለ ወይም ሆን ብሎ ላለመተግበር የወሰነ እንደሆነ ነው።

፩ኛ/ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተለይም ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን የጥሰት አይነቶች በአግባቡ መመርመር እና ማጣራት ሳይችል ሲቀር፣

፪ኛ/ የሰብአዊ መብት ጥሰት በመፈጸም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች ላይ ክስ ሳይመሰርት፣ የፍትህ ሂደት ሳያካሂድ እና በፈጸሙት ወንጀል ወይም ጥፋት ልክ እንዲቀጡ ሳያደርግ ሲቀር፣

፫ኛ/ የመብት ጥሰት የተፈጸመባቸው እና በጥሰቱም የጉዳት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች ተገቢውን ፍትሕ ሳይሰጥ እና በጉዳታቸውም ልክ እንዲካሱ ሳያደርግ ሲቀር እና

፬ኛ/ ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ተገቢ የሆኑ የቅድመ መከላከል ሥራዎችን ሳይሰራ የቀረ እንደሆነ ነው።

በተባበሩት መንግስታት ጸድቆ የወጣውና ተጠያቂነትን የሚያጸናው የመርህ ሰነድ ዋና መነሻው እና ትኩረቱ በእነዚህ አራት የመንግስት ኃላፊነቶች ላይ የተመሰረተ ነው። በጥቅሉ ይህ የመርህ ሰነድ ሌሎች መሰረታዊ የሆኑ እና ሰብአዊ መብቶችን በአንድ አገር ለማስከበር እንደ ዋልታ የሚቆጠሩ መብቶች፤ ፍትሕ የማግኘት መብት፣ እውነቱን የማወቅ መብት፣ ትክክለኛ የመፍትሔ እርምጃ እና ካሳ የማግኘት መብት፣ የተደጋጋሚ ጥቃት ሰለባ ላለመሆን ዋስትና የማግኘት መብት ላይም የተመሰረተ ነው። እነዚህ አራት የመንግስት ኃላፊነቶችን በአግባቡ ለመወጣት ደግሞ እያንዳንዱ ሃገር አራት ዋና የአሰራር ሥልቶችን ተቋማዊ በሆነ ቅርጽ ሊያከናውን ይገባል። እነሱም፤

ሀ/ የፍርድ ሂደት፤ በአገር ውስጥ፣ በአለም አቀፍ እና ከአገር ውጭ ባሉ እና ሥልጣኑ ባላቸው የፍትሕ መድረኮች አጥፊዎች የሚጠየቁበትን ተቋማዊ አሰራር መዘርጋት፣

ለ/ እውነትን የማፈላለጊያ መንገዶችን መዘርጋት፤ የእውነት አጣሪ ኮሚሽን ወይም ሌላ የመረጃ አሰባሳቢ እና አጣሪ አካል ማቋቋም እና መረጃዎችን በአግባቡ መሰብሰብ እና መሰነድ፤

ሐ/ ካሳ፤ የመብት ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የመልሶ ማቋቋሚያ፣ የገንዘብ ድጋፍ፣ የሕክምና አገልግሎቶች የሚያገኙበትን እና በይፋ ይቅርታ የሚጠየቁበትን አሰራር መዘርጋት፤

መ/ ተቋማዊ ለውጦች፤ የፍትህ እና የጸጥታ ተቋማት ላይ ያተኮረ የለውጥ ሥራዎችን በመስራት ተቋማቶቹ ሥራቸውን ነጻና ገለልተኛ ሆነው እንዲሁም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ እንዲሰሩ በሚያስችል መንገድ ማዋቀር፣ ጥብቅ ክትትል ማድረግ፣ ተጠያቂነትን ማስፈን እና ቀደም ሲል በእነዚህ ተቋማት ውስጥ በመብት ጥሰት የተሳተፉ ኃላፊዎችን እና ባለሙያዎችን በማሰናበት ተቋሞቹ የሕዝብ እምነት የሚጣልባቸው እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

አንድ እንደ ኢትዮጵያ ያለ እና ለረዥም አመታት በከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት ውስጥ የቆየ አገር ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር፣ ተጠያቂነት እና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት መንግስታዊ ሥርዓት ለማዋቀር ከላይ የተጠቀሱትን ተቋማዊ ሥራዎች በብቃት ማከናወን እንደ ዋና እና መሰረታዊ እርማጃ ይቆጠራል። ይህ አይነቱ አሰራርም የሽግግር ወቅት ፍትህን ለማስፈን ከመርዳትም ባሻገር በሚካሄደው ለውጥ ላይ ሕዝብ አመኔታ እንዲኖረው እና ለውጡም በጽኑ መሰረት ላይ እንዲቆም ያደርጋል።

## ኢትዮጵያ ውስጥ ከተጠያቂነት የማምለጥ ልማድ

ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች በገፍ ከሚጣሱባቸው እና የመንግስታቶቻቸው በሰብአዊ መብት አያያዝ እረገድ በአለም አቀፍ መድረኮች በከፍተኛ ሁኔታ ከሚወቀሱት አገሮች በግንባር ቀደምነት ስትጠቀስ ኖራለች። ባለፉት ሦስት አመታት ውስጥ በአገሪቱ የተከሰተውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ አንዳንድ በጎ የሚባሉ እና በሰብአዊ መብት አያያዝ እረገድ መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም የዛኑ ያህልም ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ግምት ሊሰጣቸው የሚሹ የመብት ጥሰቶችንም አስተናግዳለች። በሚሊዮኖን የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በእርስ በርስ ግጭቶች እና ዘር ላይ ባነጣጠሩ ጥቃቶች ሕይወታቸው ጠፍቷል። ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የዜጎች ንብረት እና የሃገር ሃብትም ሊወድም ችሏል። ኢትዮጵያ በሰብአዊ መብቶች ጥሰት መበራከት ብቻም ሳይሆን በአለም አቀፍ መድረኮች የምትታወቀው እና የምትወቀሰው፤ አጥፊዎችን ለፍርድ በማቅረብ እረገድም ከደረሰው የጥሰት ስፋት አንጻር ግምት የሚሰጠው ወይም ሚዛን የሚደፋ እርምጃ ባለመውሰድም ትታወቃለች።

ለእዚህም በዋና ማሳያነት የሚጠቀሰው ባለፉት ሃያ ሰባት አመታት በአገሪቱ ውስጥ በዜጎች ላይ አስከፊ የመብት ጥሰት የፈጸሙ፣ ያስፈጸሙ እና እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ያመቻቹ ወይም በመብት ጥሰቶች ውስጥ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ተሳትፎ የነበራቸው የመንግስት ባለሥልጣናት፣ የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊዎች፣ የፖሊስ እና የመከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ በግልጽ የተወሰደ ምንም አይነት እርምጃ አለመኖሩ ነው። በመቀጠልም በእነዚህ አካላት ላይ አሁንም የጥፋታቸውን ደረጃ እና አይነት በገለልተኝነት የሚመረምር እና የቀጣይ እርምጃ ሃሳቦችን የሚያፈልቅ ኮሚሽን ወይም የመረጃ አሰባሳቢ አካል አለመኖሩ አሁንም ኢትዮጵያ አጥፊዎችን ከለላ የመስጠት ወይም ከተጠያቂነት ነጻ እንዲሆኑ የሚያደርገውን ልማድ መቀጠሏን ያመላክታል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ለሦስት አሥርት አመታት በሚጠቃ እድሜ ውስጥ በርካታ የመብት ጥሰቶችን ሲመረምር፣ ማስረጃ ሲያሰባስብ እና በአግባቡ ጠርዞም መግለጫዎችን ሲያወጣ ቆይቷል። በኢሰመጉ መግለጫዎች ውስጥ በተካተቱት የመብት ጥሰቶች ላይ ቀጥተያ ተሳታፊ የሆኑ አካላት እና ግለሰቦች ለፈጸሙት የወንጀል አድራጎት ወይም የሕግ መተላለፍ በመንግስት በኩል እርምጃዎች አልተወሰዱም። ወደፊት እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚችሉም የሚያመላክቱ ነገሮች በግልጽ አይታዩም። መንግስት በዚህ እረገድ የሕግ ተጠያቂነትን በማስፈን፣ አጥፊዎችን ለፍርድ በማቅረብ እና ተበዳዮችን ለመካስ የተጣሉበትን አለም አቀፍ ግዴታዎች በአግባቡ ለመወጣት ያለውን ቁርጠኝነትም ሆነ ዝግጅት የሚያሳዩ ፍንጮች የሉም።

ይህ አለመሆኑ ደግሞ አገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዲኖር፣ አጥፊዎች ከጥፋታቸው ሳይማሩ ሌሎች አዳዲስ ጥፋቶችን በከፋ ሁኔታ እንዲፈጽሙ በማድረግ እና ተበዳዮችም ከሌላ አዳዲስ ጥቃት እንዲጠበቁ አላደረገም። በዚህም ሳቢያ አገሪቱ ውስጥ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው እና ተመሳሳይ አጥፊዎች የሚሳተፉባቸው የመብት ጥሰቶች በተደጋጋሚ እና እጅግ በከፋ ሁኔታ እንዲፈጸሙ ምክንያት እየሆነ ነው። መንግስት ተቀብሎ ባጸደቃቸው የአለም አቀፍ ስምምነቶች፤ በተለይም በአለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ ፪ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው መንግስት ሰብአዊ መብቶችን በማስጠበቅ እና በማረጋገጥ እረገድ ሁለት የተጣሉበትን ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት ግዴታ አለበት።

Article 2 of the ICCPR, “[a] general obligation is imposed on States Parties to respect the Covenant rights and to ensure them to all individuals in their territory and subject to their jurisdiction [...] [and that this legal obligation] is both negative and positive in nature.”[1]

የመጀመሪያው ግዴታ ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እና በቂ እውቅና መስጠት ነው። ሁለተኛው ኃላፊነት ደግሞ እነዚህ መብቶች እንዳይጣሱ በቂ ጥበቃ ማድረግ ነው። በቂ ጥበቃ ለማድረግ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን አራት መሰረታዊ የሆኑ እና ለጥፋት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ መወሰድ የሚገባቸው፤ ጥሰቶች ላይ በቂ ምርመራ ማካሄድ፣ አጥፊዎችን በሕግ ጥላ ስር አዎሎ ተጠያቂ ማድረግ፣ ለተጎጂዎች በጉዳታቸው ልክ ተመጣጣኝ ካሳ መስጠት እና ይቅርታ መጠየቅ፤ እንዲሁም ተመሳሳይ የጥፋት እርምጃዎች እንዳይፈጸሙ የቅድመ መከላከል ሥራዎችን መስራት ይኖርበታል።

1 International Law and the Fight Against Impunity, A practical Guide, International Commission of Jurists,
https://www.icj.org/wp-content/uploads/2015/12/Universal-Fight-against-impunity-PG-no7-comp-Publications-Practitioners-guide-series-2015-ENG.pdf

## ማጠቃለይ

መንግስት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስድስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች በአግባቡ እንዲወጣ ማበረታታት እና መደገፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ተቀዳሚ ሥራ ሊሆን ይገባል። እነሱም፤

ሀ/ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ቅድመ መከላከል ሥራ የመስራት ግዴታ (The obligation to prevent human rights violations);

ለ/ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በተፈጸሙ ጊዜም ጉዳዩን በአፋጣኝ የመመርመር እና ማስረጃዎችን የመሰብሰብ ግዴታ (The obligation to investigate human rights violations);

ሐ/ አጥፊዎችን ወደ ፍትሕ የማምጣት እና ለጥፋቱ ኃላፊ የሆኑ ግለሰቦች በቂ ቅጣት እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታ (The obligation to bring to justice and punish those responsible for these abuses);

መ/ የመብት ጥሰት ለተፈጸመባቸው ሰዎች ተገቢውን እና አመርቂ የሆነ የመፍትሔ ወይም የማካካሻ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ (The obligation to provide an effective remedy to the victims of human rights violations);

ሠ/ ለመብት ጥሰት ተጎጂዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ለጉዳታቸው መካሻ የሚሆን ተመጣጣኝ ማካካሻ የመስጠት ግዴታ (The obligation to provide just and adequate reparations to the victims and their family members); እና

ረ/ ስለተፈጸሙት የመብት ጥሰቶች እውነት የሆነው ነገር ወይም ትክክለኛው ታሪክ በአግባቡ እንዲታወቅ እና እንዲገለጽ የማድረግ ግዴታ (The obligation to establish the truth about what happened) ናቸው።

ኢትዮጵያ እነዚህን አለም አቀፍ ግዴታዎቿን በአግባቡ ለመወጣት ብዙ እርቀቶችን መጓዝ ይጠበቅባታል። የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላት ዛሬም የማይጠየቁበት ወይም በጥፋታቸው ልክ የማይቀጡበት ወይም የሰሩት ጥፋት በአግባቡ እና በገለልተኛ አካል ተጣርቶ እውነቱ እንዲወጣ የማይደረግበት ሂደት እና ልማድ አሁንም ጎልቶ ይታያል። አልፎ አልፎ የሚታዩ እና የሚበረታቱ አንዳንድ በጎ እርምጃዎች ቢኖሩም ብዙ ሥራዎች ግን ገና ትኩረት እንዳላገኙ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል። አጥፊዎችን ተጠያቂ የማያደርግ መንግስታዊ አሰራር ባለበት አገር ሁሉ ሰብአዊ መብቶችን በአግባቡ ማስከበር አይቻልም።

ሐምሌ 29 ቀን 2020 ዓ/ም (እ.ኤ.አ)

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ኬላ

ሕግ

# የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሰብዓዊመብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ዐዋጅ አዳዲስ ነጥቦች

ጥበቡ ኃ.

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለፈው ሐምሌ 7 ቀን 2012 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን የቀድሞውን ዐዋጅ ቁጥር 290/1992 የሚያሻሻል ዐዋጅ ማጽደቁ ይታወሳል፡፡ ዛሬ በ ‹‹ኬላ›› አምዳችን ሥር ይኸው ዐዋጅ ምን አዲስ ነገር አስተዋወቀ፣ ከቀድሞው ዐዋጅስ በምን ይለያል የሚሉትን ነጥቦች በአጭሩ እንደሚከተለው እናያለን፡፡

የማሻሻያ ዐዋጁ የቀድሞውን ዐዋጅ ለምን ማሻሻል እንዳስፈለገው በማርቀቅ ሒደቱ ወቅት የተዘጋጀው ማብራሪያ ሰነድ ‹‹ዐዋጁ ከጸደቀ ከ20 ዓመት በላይ የሆነው በመሆኑ፣ እስከ አሁን ከነበረው አሰራር የተገኙ ልምዶችን ከዓለም አቀፍ መርሆዎች እና ከሀገራችን የለውጥ ሂደት አንጻር የዲሞክራሲ ተቋማትን ነጻ፣ ገለልተኛና፣ ውጤታማ እንዲሆኑ አድርጎ በማደራጀት የተቋሙን ተዓማኒነት እና የማስፈጸም አቅም ለማሰደግ፣ ከዓለም አቀፍ ልምዶች፣ የሰብዓዊ መብት መርሆዎች፣ እንዲሁም ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት ተቋማት እንዲያሟሉ የሚገባቸውን መስፈርቶች በመፈተሽ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የተጣጣሙ ሆነው ለማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ነው›› ሲል ይገልጸዋል፡፡

በዚሁ ቅኝት ዐዋጁ በመግቢያው ላይ ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን ሰብዓዊ መብቶችን የማስፋፋት፣ የማስጠበቅ እና የማስከበር ሥራ በተገቢው መንገድ እንዲያከናውን ለማስቻልና የማስፈጸም አቅሙን ለማሳደግ፣ የኮሚሽነሮችን አመራረጥ ብቃትና አቅምን ከግምት ያስገባ ብሎም አሳታፊና ግልጽ ለማድረግ፣ የተቋሙን ተዓማኒነት፣ ተቀባይነት እና ውጤታማነት ለማጎልበት፣ የተቋሙን መዋቅር፣ የሠራተኛ ቅጥርና አስተዳደር እንዲሁም የበጀት ነጻነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የቀድሞውን ዐዋጅ ድንጋጌዎች ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ የማሻሻያ ዐዋጁ የተዘጋጀ መሆኑን ይገልጻል፡፡

የኮሚሽኑን ሥልጣን እና ተግባር በሚመለከት በተሻሻለው ዐዋጅ አንቀጽ 6 ሥር ተዘርዝረው ከነበሩ ነጥቦች በተጨማሪ የማሻሻያ ዐዋጁ አዳዲስ ሥልጣን እና ተግባራት አካትቶ ይዟል፡፡ እነዚህም፡

- በአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ወቅት ስለ ሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ሁኔታ ክትትል ማድረግ (አንቀጽ 6/12)፣ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውንም ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች ወይም በቁጥጥር ወይም በእገታ ሥር የሚገኙ ሰዎች ያሉበት ሥፍራ፣ እንዲሁም ትምህርት ቤትና መጠለያ ጣቢያዎችና ሌሎች ሥፍራዎች ያለ ቅድመ ማስታወቂያ መጎብኘት (አንቀጽ 6/13) የሚሉት ናቸው፡፡ የእስር ቦታዎችን ያለ ቅድመ-ማስታወቂያ መጎብኘትን የሚመለከተው ማሻሻያ በዓለም አቀፍ መድረኮች በተደረገ ግምገማም እንደ ክፍተት ታይቶ እንዲሻሻል ምክረ-ሐሳብ የቀረበበት ጉዳይ በመሆኑ መልካም እርምጃ ነው፡፡

በረቂቅ የማሻሻያ ዐዋጁ ላይ ‹‹በምርጫ ወቅት በምርጫ ታዛቢነትና በሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ክትትል ማድረግ›› የሚል ነጥብ ተካትቶ የነበረ ቢሆንም፤ ም/ቤቱ ኮሚሽኑ በሌሎች ሥራዎች ላይ በትኩረት እንዲሠራ አያደርገውም በሚል በጸደቀው የማሻሻያ ዐዋጅ ላይ ሳይካተት እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ምርጫ ሰብዓዊ መብት እንደመሆኑ እና በሀገራችን ቀደም ብሎ ከታዩት የምርጫ ልማዶች አንጻር ኮሚሽኑ በታዛቢነት እንዳይሳተፍ ማድረጉ አጥጋቢ ምክንያት አይመስልም፡፡ ይህም የማሻሻያ ዐዋጁ ከሚተችባቸው ዋነኛ ነጥቦች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡

የኮሚሽነሩን እና የምክትል ኮሚሽነሮችን አደረጃጀት በተመለከተ በተሻሻለው ዐዋጅ አንቀጽ 8/2/መ ሥር ‹‹ሌሎች ኮሚሽነሮች›› የሚለው ‹‹ሌሎች ከአራት ያላነሱ የልዩ ልዩ ሰብዓዊ መብቶች ዘርፍ ጉዳዮችን የሚመሩ ኮሚሽነሮች›› በሚል እንዲተካ ተደርጓል፡፡ ይህም ማሻሻያ ትኩረት ተሰጥቷቸው፣ መፍትሔ የሚያሻቸው ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘርፎች (Thematic Areas) በሙያው ልምድ እና ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች በመታገዝ ለማስተካከል ይረዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በተመለከተ በቀድሞው ዐዋጅ አንቀጽ 9 ሥር ከተቀመጠው በተለየ የማሻሻያ ዐዋጁ ኮሚሽኑ በኮሚሽነሮች ጉባኤ ውሳኔ ሰጪነት መሠረት በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም አቤቱታ መቀበያ ማዕከሎች ይኖሩታል በሚል አሻሽሎታል፡፡ የኮሚሽነርነት ሹመት መመዘኛዎችን በተመለከተ «የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ» የሚል አዲስ መስፈርት ያስተዋወቀ ሲሆን፤ በቀድሞው ዐዋጅ አንቀጽ 12/7 ሥር ነበረውን «ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው» የሚለውን መስፈርት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ይህም አካል ጉዳተኞችን አግላይ እንዳይሆን በማድረግ መሻሻሉ በመልካም ጎኑ ይታያል፡፡

የኮሚሽነሮችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን በተመለከተ የማሻሻያ ዐዋጁ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ኮሚሽነር እና ሌሎች ኮሚሽነሮች እንደየደራጃቸው በሚንስትር፣ ምክትል ሚንስትር እና ዋና ዳይሬክተር ማዕረግ ላሉ የመንግሥት ተሿሚዎች የሚሰጡ መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞችን እንደሚያገኙ ይደነግጋል (አንቀጽ 18/1)፡፡ ተሿሚዎቹ ልዩ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ በሚችሉበት እና የጥቅም ግጭት የማይፈጥሩ ሌሎች ሥራዎች ላይም በትርፍ ሰዓታቸው ሊሰማሩ እንደሚችሉም ይደነግጋል (አንቀጽ 18/2)፡፡

በቀድሞው ዐዋጅ የማስረጃ አቀራረብን የተመለከተው ድንጋጌ ሥር የማሻሻያ ዐዋጁ ስለ ምስክሮች ጥበቃ አዲስ ንዑስ አንቀጽ እንዲጨመር አድርጓል፡፡ ይህም ማስረጃ በማቅረብ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ለሚሆኑ ምስክሮች በፍርድ ቤት ለሚቀርቡ ምስክሮች የሚሰጣቸውን ዓይነት የሕግ ከለላ እና ጥበቃ በኮሚሽኑ ሥር ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ለሚሰጡም ምስክሮች እንዲሰጥ የሚያደርግ ማሻሻያ ነው፡፡

የኮሚሽኑን የፋይናንስ እና የአስተዳደር ነጻነትን ለማረጋገጥ ያስችላሉ ከተባለላቸው የማሻሻያ ድንጋጌዎች ሌላኛው በጀትን የተመለከተው ነው፡፡ በዚህም መሠረት የዐዋጁ አንቀጽ 36/2 ምክር ቤቱ ለኮሚሽኑ ያጸደቀለትን ዓመታዊ በጀት የገንዘብ ሚንስቴር ወደ ኮሚሽኑ የባንክ አካውንት ሙሉ በሙሉ በሦስት ወር ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርበት ደንግጓል፡፡

.../...

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ቀለም

## ተስፋ



ፎቶ የሻሸመኔ ወጣቶች

ከነ ክንብንባችን ከነ አዳፈው መጎናጸፊያችን፣ ከነ ዝክንትላችን ዘመን ሊቀየር ነው። እንኳን አደረሰን እንኳን አደረሳችሁ።

ዘመን ጥሩ ነው ክፉንም ደጉንም ያሳየናል በተለይ ወለምታችንን ታሽተን ቁስላችን ሽሮ ቢሆን ደግሞ ማን እንደ ዘመን! ካሮጌ ቁስል ላይ በየዘመኑ አዲስ ቁስል ለምንጨምር ለ እኛ ግን እዳ እየተከመረ በአዲስ አመትም በ ህመም የጎበጠ ዘመን ተሸክመን ለመሻገር እንገደዳለን።

ባልታረመ ማንነት እና አሁንም ባልጠራ ሀገራዊነት ለምንሻገር ለእኛ ግን መስራት የነበረብን ብዙ የቤት ስራዎች ይዘን ወደ አዲሱ አመት ልንሻገር ነው።

2012 ብዙ አቅደን ብዙ ሞክረን በብዙ ደግሞ የተፈተንበት ዐአመት ሆኖ አልፏል። በዚህ አመት ማገባደጃ ላይ ሆነን ስናስበው ያለፈው አመት ብዙ ውጣውረዶች ብዙ መፈናቀል፣ ብጥብጥ፣ ግድያ፣ ጥላቻ፣ ሁከት፣ ኮሮና በየተራ ሲያምሱን ተረጋግተን ለማሰብ እና ስህተቶቻችንን ለማረም አፍታ ጊዜም አልሰጡን።

ይሁን እንጂ በብዙ ወደ ኋላ ቀርቶ ሀላፊነት እንዳለበት ህዝብ የሚቀጥለው አመት የተረፈ ጊዜ እና ቅንጦት አይኖረንም። ብዙ እምናስተካክላቸው ነገሮች አሉ።

ምርጫን ያክል ትልቅ ነገር ከፊታችን ይጠብቀናል አሁንስ እንደ ሀገር ምን ያህል ተዘጋጅተናአል እሚለውን ልባችን እያወቀው

ከምርጫ በፊት ማድረግ ይኖርብናል ብየ ያሰብኩትን ልናገር

## ሀገራዊ እርቅ

ለሀገራችን ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ አሁን ላይ ሀገራዊ እርቅ እና መግባባት ያስፈልገናል። በደፈናው ሳይሆን በዳይ እና ተበዳይ ፊት ለፊት በአደባባይ እየተያዩ በደሉን ጠቅሶ በይፋ ይቅራታ መባባል አለብን።

መንግስት ከህዝብ ጋር፣ህዝብ ከመንግስት ጋር፣ ህዝብ ከህዝብ ጋር፣ የሀይማኖት አባቶች ከህዝብ ጋር ይቅርታ መጠያየቅ አለባቸው።

በ እኔ እበልጣለሁ እና ባለጊዜ ነኝ ትርክት፣ በተጎጂነት እሳቤ እና በተሸናፊነት ስሜት ወደፊት አንድ እርምጃ መራመድ የለብንም። ከ አሁን ቀደም አደረግነው ያልነውን የተድበሰበሰች እና የጨዋታ ይቅርታችንን ወደጎን ትተን አብሮ ለመቀጠል ነጋችንን አንድ ላይ ለመተለም ከልብ የሆነ እውነተኛ ይቅርታ ማወጅ ይኖርብናል።

ሀገራችን ያጠፉ እማይቀጣባት እና የተጎዳ ፍትህ አልባ ሆኖ እሚኖርባት ሀገር ከሆነች ቆይታለች። ይህ ካልተቀየረ ሁሉም ሰው በሀገሩ የፍትህ ስራት ተስፋ ካጣ የሰላም ሚንስቴር ማቋቋም ብቻውን ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ ይሉት ነገር ይሆንብና የናፈቅነው ሰላም እንደ ህልም እንጀራ እያመሰኩ ባዶ ይሆንብናል።

በዚህ አዲስ አመት ይህን አድርገን በተስፋ እንጀምረው ይቅር እንባባል። የሁሉም መኖር ለሁሉም ይጠቅማል እና ያለፈውን ቁርሿችንን ወደጎን ብለን ነገ ለምናስባት ኢትዮጵያ እንያያዝ የሁላችንም መኖር እኩል ዋጋ አለው እና በ እኩልነት እንሰለፍ። ተስፋ አለ ሁሉም ኢትዮጲያዊ በአንድነት ሀገሬ እሚላትን ሀገር እንገነባለን።

ለሁሉም ቦታ ያላትን ሀገር ለመገንባት ትልቁ መነሻ ይቅርታ ነው። ያለፈን ረስቶ ለነገ መነሳት ያደፈውን መጎናጸፊያችንን አጥበን በፍቅር ቀና ማለት እንችል ዘንድ ምኞቴ ነው።

ሰላም




ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።